የሰ/መ/ቁ. 28130

2/09/98

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ የወረዳ 10 ቀበሌ 15 ሀብረት ሱቅ

ተጠሪ፦ አቶ ብርሃኑ ተሠማ

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ የ12 ዓመት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው በመወሠኑና ይህንኑ ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ ነው።

ተጠሪ በፌ/መ/ደ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች የሥራ ውላቸውን ከሕግ ውጪ በማቋረጡ ወደ ሥራ እንዲመልሣቸው የማይመልሣቸው ከሆነም የ12 ዓመት የአመት ፈቃድን ጨምሮ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን አረጋግጦ 12 ዓመት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሁም ሌሎች ይገባቸዋል ያለውን ክፍያዎች ወስኗል። የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለተጠሪ የ12 ዓመት የአመት ፈቃድ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ አጽድቋል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ተጠሪ ቀርበው ችሎቱ የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር መርምሯል።

በዚህም ጉዳይ አከራካሪ የሆነው አንድ ሠራተኛ 12 ዓመት የተጠራቀመ የአመት ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል ወይ? የሚለው ነው።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 21/10/98

አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃድ ከክፍያ ጋር የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 77/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛውም ይህንን የአመት ፈቃድ በየአመቱ የማግኘት መብት ያለው መሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 78/1/ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ሠራተኛው በየአመቱ የአመት ፈቃድ የማግኘት መብት ያለው ቢሆንም ከአሠሪው ጋር በመስማማት ወይም አሠሪው የሥራ ሁኔታ ሲያስገድደው የሠራተኛው የአመት ፈቃድ ወደ ሌላኛው አመት ሊተላለፍ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 79/2/ እና /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ግን በነዚህ ንዑስ ቁጥሮች ሥር በተመለከቱ ሁኔታዎች የአመት ፈቃድ ሊተላለፍ የሚችል ቢሆንም የተላለፈው የአመት ፈቃድ ከሚቀጥለው ሁለት ዓመት በላይ ሊራዘም የማይችል ለመሆኑ አንቀጽ 79/5/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የአንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃድ ሊተላለፍ የሚችለው ቢበዛ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ሠራተኛው የአመት ፈቃዱን እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልጠየቀ ከዚያ በኋላ ሊጠይቅ የሚችልበት የሕግ መሠረት የለውም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ ተጠሪ የጠየቁት የ12 ዓመት የአመት ፈቃድ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጥያቄያቸውን እንዳለ ተቀብሎ ወስኖላቸዋል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ግን በአ/ቁ 42/85 መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን የአመት ፈቃድ ሠራተኛው የማግኘት መብት የሌለው በመሆኑ የፍ/ቤቱ ውሣኔ የአዋጁን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 2469 በ14/04/96 እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 30960 በ12/11/96 አመልካች ለተጠሪ የ12 ዓመት የአመት ፈቃድ እንዲከፈል የሠጡት የውሣኔ ክፍል ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከሥራ ከመሠናበታቸው በፊት የነበራቸው የመጨረሻው ሁለት ዓመት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ይከፈላቸው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ስለተዘጋ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 21/10/98

ነ/ዓ